# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

# Ethiopian People's Revolutionary Party(EPRP)

ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም

ይድረስ፡-

ለአገዛዙ የጦር ኃይሎች፡ ለፖሊስ ሠራዊትና ለደህንነት ተቋም አባላት ሁሉ

በተለያዩ ምክንያቶች የነዚህ ተቋማት አባል በመሆን ተሰማርታችሁ ያላችሁት ሁሉ በመሠረቱ ሙያችሁ ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ አካል የህዝብ አገልግሎት ሰጪዎች፤ የሀገር ዳር ድንበር አስከባሪዎች፤ የሰላም፣ የደህንነትና የፍትህ ጠባቂዎች ሆናችሁ መገኘት ነበር። የሀገር ነጻነት፣ የሕግ የበላይነት፣ የሕዝብ እኩልነት፡ ፍትህ፡ ሰላምና ብልጽግና በሀገራችን ቢኖር እናንተም ለዚህ ቀና አላማ የበኩላችሁን አስተዋጽዖ ብታበረክቱ ተጠቃሚው የሀገሪቱ ዜጋ በሙሉ ሲሆን፤ ለሁላችንም ደስታና ኩራት በሆነ ነበር። የዜግነት ግዴታችሁንና ኃላፊነታችሁን መሠረታዊነት ያለው ታሪክ እንድትሠሩ ትውልድ የሚጠብቅበት ወቅት ሆኖ ሳለ ያለመታደል ሆኖ ከ18 አመት ጀምሮ እያገለገላችሁት ያለው ቡድን እናንተን በመጠቀምና የራሱ ተገን አድርጎ በመቁጠር አስተዳድረዋለሁ የሚለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎሳ እየከፋፈለ፥ እያሰቃየ፥ እየበደለ፥ እያሳሰረና እያስገደለ፤ የተወሰኑትንም ደግሞ ደብዛቸውን እያስጠፋ ሀገርን እያስገነጠለ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር የሚያውቀው ነውና በናንተ ቢከፋ፡ ቢቀየም የሚያስገርም አለመሆኑን ታጡታላችሁ የሚል ግምት አይኖረንም።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተለይም ከ1997 ግንቦት ምርጫ ማግስት በአግአዚ ጦር በአዲስ አበባ ብቻ ከ200 በላይ የሚሆኑ ንጹሃን ዜጎችን አስጨፍጭፎ፥ በጋምቤላ፥ በኦጋዴን...ወዘተ በዓለም ፍርድ ቤት የሚያስጠይቁ አሰቃቂ የጅምላ እርምጃዎች ምክንያት የስንቱ ቤተሰብ እንደተናጋ፣ ስንቱ ወላጅ ልጆቹን እንዳጣ፣ ስንቶቹን ሕጻናት ያለ አሳዳጊ እንዳስቀረና በየቦታው መውደቃቸው፤ ስንቶቹን ከድህነት ወለል በታች፣ ስንቶቹን በፍርሃትና በሰቀቀን ለመኖር እንዳስገደዳቸው፤ በዘርና በጎሳ እንዲከፋፈሉ አድርጎ በገዛ ሀገራቸው ለባይተዋርነት እንደዳረጋቸው ከግልጽም ግልጽ ነው። ይህ መቀጠል ስለማይኖርበት፤ ቆም ብላችሁ ሕሊናችሁን ከፍታችሁ፣ ልቦናችሁን ግልጽ አድርጋችሁ በጫንቃችሁ ላይ ተቆናጦ ለመሰሪ ድርጊት መጠቀሚያ ከመሆን ለመውጣት በጥሞና ለመመርመርና መፍትሄም ለመሻት፤ የራሳችሁንም ሚና ለመወሰን የምትችሉበት ወቅት አሁን ነው ብንል ሀቁን መናገር እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም ይህንን ማሳሰቢያና ጥሪ በአሁኑ ጊዜ ለናንተ ማቅረቡ አግባብነት ያለው ይሆናል።

ከሕዝብ ባይተዋር ሆናችሁ ተሰውራችሁ በጦር ሠፈራችሁና በየመሥሪያ ቤታችሁ የተወሸቃችሁ/የታጎራችሁ ሳትሆኑ በቀን ተቀን ኑሯችሁ ከዘመድ አዝማዶቻችሁ በተለይም ከቅርብ ቤተሰቦቻችሁ የምትገናኙ ናችሁና እነሱም ሆኑ አጠቃላይ ሕዝቡ በምን አይነት አሳዛኝና አሰቃቂ ኑሮ ለመኖር የተገደደ መሆኑን የምታዩትና የምትገነዘቡት ነው። የሕዝቡ ሁኔታ ደስታ ሳይሆን ጭንቀትንና ሀዘንን፤ ነጻነትን ሳይሆን በደልን፤ የኑሮ መደላደል ሳይሆን መመሰቃቀልን፣ መራዝና መጠማትን የሚያሳይ መሆኑን ሕሊናውን ማሳወር ለሚፈልጉ ጥቂቶች በመካከላችሁ ከተወሸቁት ሆድ አምላኩ ከሆኑትና ሰብዕናቸውን ለአገዛዙ ከሸጡት በስተቀር ለብዙዎቻችሁ ግልጽ ይመስለናል። የመለስ አገዛዝ ሀገር ድንበር እንድታስከበሩ ሳይሆን የሱን የሥልጣን እድሜ ማራዘሚያ አድርጎ የልጆቻችሁን፥ የወላጆቻችሁን፣ የእህቶቻችሁንና የወንድሞቻችሁን ንጹህ ደም በግፍ እንድታፈሱ እየተጠቀመባችሁ መሆኑን ከናንተ የተሰወረ ሁኔታ አይደለም። የሥራ ባልደረቦቻችሁ የነበሩት ከመካከላችሁ ጠፍተው ለስደት የተዳረጉት በየጊዜው የሚያሰሙት እሮሮ ይህንኑ የሚገልጽ እንጂ ሌላ አይደለም። በሹመት፥ በሥራ ድልድል፥ በደሞዝ ጭማሪ፥ ከቦታ ቦታ መዘዋወር የሚደረግባችሁን አድልዎ በመቃወም የምታደርጉት የውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴ የሚመሰክረው ይህንኑ ነው። የበላይ አዛዥ እንዲሆኑ በላያችሁ ላይ የሚሾሙባችሁ በሙስና የተጨማለቁ ከመሆናቸው ባሻገር በችሎታ፥ በእውቀት፥

በትምህርት ባገኙት ተመክሮ ተመዝነው ሳይሆን ከአንድ ጎሳ ተመርጠው፤ ለቡድኑ ባላቸው ታማኝነት እየተገመገሙ በመሆኑ በሥራችሁ ላይ የሚያደርሷቸው ጉድለቶችና ጥፋቶች ምንኛ እያስመረሯችሁ እንዳሉ የምንገነዘበው ነው። ያጉረመረሙ፣ ጥያቄ ያቀረቡ በየምክንያቱ በስውር እየተለቀሙ፤ የሚረሸኑትና የሚታሰሩት ቁጥራቸው በርካታ መሆኑን የምታጡት አይደላችሁምና ነግ በኔ በማለት ተደራጅታችሁ ይህንን አደጋ ከሕዝብ ጋር ከመቋቋም ውጭ ሌላ አማራጭ የላችሁም። ይህ ደግሞ በደርግ ጊዜም ለውድቀት የዳረገ አካሄድ መሆኑን የምትረሱት ሳይሆን እንዲያውም በዚህ ሁናቴ ለመገኘት ከመብቃታችሁ በፊት እውቀት ልትገበዩበት የሚገባ በሆነ ነበር።

የባዕዳንን አጀንዳ ለማስፈጸም ሲባል በጎረቤት ሶማሊያ የውስጥ ችግር ጣልቃ እንድትገቡ አዘምቶ ለሕሊና የሚሰቀጥጥ ድርጊት እንድትፈጽሙ በመገደዳችሁ ምስጋናና ከበሬታ ሳይሆን ጥላቻን አተረፋችሁ። በተጨማሪም ደግሞ በቅርብ ጊዜ ሊፋቅ የማይችል የጠላትነት ስሜት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንዲስፋፋ በሶማሊያ የተፈጸሙት ድርጊቶች ምክንያት ሊሆኑ በቅተዋል። አብረዋችሁ በዚህ የወያኔ ግዳጅ ለሕይወተ ሕልፈት የተዳረጉ የሥራ ባልደረቦቻችሁ ቁጥር እንኳ በይፋ አልተነገራችሁም። በጦር ሠራዊት ደንብም ሆነ በባህላችን መሠረት በቤተሰቦቻቸው የመቀበር እድሉን ያላገኙት ስንቶች እንደሆኑ ስናሰላስል ሀዜኔታችን የከበደ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ከግዳጅ መልስ ስንቶቻችሁ ተገቢውን እንክብካቤ እንዳላገኛችሁ የምታውቁት ነው። ለአካለ ስንኩልነት፣ ለሕሊና ጸጸት ተዳርጋችሁ፤ አያት ቅድመ አያቶቻችሁ ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ያስከበሩት ዳር ድንበርን ለመጠበቅና ከወራረራ ለመከላከል ሳይሆን ሌላው ቢቀር በቅርቡ በባድሜ የተነሳ እንኳ ከ70000 በላይ የሚሆኑ ዜጎቻችን በአውላላ ሜዳ ላይ ለሞት የተዳረጉት፣ ኢትዮጵያዊያን በላያቸው ሳር የበቀለበባቸው፤ ሰውነታቸው በጥይት የተበሳሳው፤ በተቀበረ ፈንጂ የሳት እራት ሆነው የቀሩት የሚረሳ አይደለም። የጦር ግባችሁን ከግብ ባላደረሳችሁበት የከፈላችሁት ከፍተኛ መስዋዕት በብጣሽ ወረቀት መና ሆኖ እንዲቀር መደረጉን ለምን ብሎ መጠየቅና ለዚህም ሃላፊ የሆነውን ቡድን ከሕግ ፊት እንዳይቀርብ መከታ እንድትሆኑ መደረጋችሁ ብቻ ሳይሆን እናንተም ራሳችሁ ብትሆኑ እንዳትጠይቁ ተሸብባችኋል። እርስ በርሳችሁ ተማምናችሁ የልባችሁን ግልጽ አድርጋችሁ እንዳትወያዩ በጆሮ ጠቢዎች ተከባችሁ እንዳትተማመኑ ሆናችኋል። ይህ በፍጹም ሊሆን የማይገባው ነገር ነው። ድንበር ጠባቂ የሚል ግዳጅ ተሰጥቷችሁ ግን ሀገር የተወሰነ አካሏ ተቆርጦ ለባዕዳን ሲሰጥ፤ ሕዝብ ከቀዬው ተፈናቅሎ ለችጋር ሲጋለጥና በባዕድ ጦር ሲባረር መታደግ ሳይሆን ለተባባሪነት ስትዳረጉ ሕዝብም ይህን አይቶ በመታዘብና በጠላትነት ቢመለከታችሁ ለምንስ ያስገርማል?

በቀጣይነት እያገለገላችሁት ያለው የመለስ አገዛዝ ከአምስት አመት በፊት በተደረገው ምርጫ ሽንፈትን ቢከናነብም የስንቱን ዜጋ ደም በግፍ አፍሶ፤ ስንቶቹን አካለ ስንኩል አድርጎ፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ደግሞ በጅምላ አፍሶና ለእስር ዳርጎ፤ ስንቶቹ የዱር አራዊትና የአዞ ሲሳይ ሆነው መቅረታቸውን በበኩላችን በቁጭትና በሰቀቀን የምናስታውሰው ነው። እናንተም ይህንን የምትረሱት ሊሆን ከቶም አይገባም። እንዲያውም ለወደፊቱ ብሩህ ተስፋ ለማምጣትና የተሻለ ኑሮ ለማግኘትም ከሕዝቡ ጋር አብሮ ለመጓዝ ለመታረቅም ምክንያት ሊሆናችሁና ሊገፋፋችሁ የሚገባ ነበር።

በቅርቡ ደግሞ ያው እንደምትመለከቱትና ለመታዘብም እንደምትችሉት የምርጫው ሂደትና ውጤት የሕዝቡን ድምጽ የሚያስከብር ሳይሆን ራሱ የመለስ አገዛዝ በቀጠይነት የሚሰየምበት ሆኖ ተፈጥሞ እንዳለፉት ሁሉ አሁንም ከዛ በከፋ ደረጃ ሕዝብንም ታዛቢንም እያተራመሰ ይገኛል። ይህ ምርጫ እየተባለ የሚጠራው የፌዝ ጨዋታ የተወሰነ የፓርላማ መቀመጫ ለማግኘት ሲባል ብቻ ፀረ ዴሞክራሲ የሆነ አገዛዝ በሥልጣኑ እንዲቀጥል ማድረግ፣ መተባበርና ሽፋን መስጠት ሀገርንና ሕዝብን ከመክዳት ውጭ ሊቆጠር አይችልም በማለት ሀገር ወዳድ ሃይሎች ለድምጸ ተአቅቦ ያቀረቡት መፈክር ከጊዜ ወደ ጊዜ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱን በደንብ ልታዩት ይገባል። በመሆኑም ሕዝብ በግዴታ ለምርጫው እንዲመዘገብ ድምጹንም እንዲሰጥ የተለያዩ ጫናዎች ቢደረግበትም ባለው አቅሙ ይህ የድምጸ ተአቅቦ

መፈክር ስኬታማ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል። ሕዝብ የእምቢተኝነት ውሳኔውን የሚገልጽበት ኃይል ለጊዜው ስለሌለው የተቀበለ መስሎ መጓዝ ግድ ቢሆንበትም የዚህን እውነታነት ግን በምንም ዓይነት የሚቀይረው አይሆንም። የመለስ አገዛዝ በሥልጣን ላይ እያለ፣ እሱና ደጋፊዎቹ እንደፈለጉት ቢያቅራሩ የምርጫ ጋጋታ ቢያካሂዱ፣ የፓርላማ መቀመጫዎች ጨመሩ አልጨመሩ፤ ተለጣፊን በሌላ ተለጣፊ ቢቀይሩ ለብዙሃኑ ሕዝባችን ጠብ የሚልለት ነገር የለም። ምናልባት እንደተለመደው ለብዙሃኑ ሕዝብ ጠብ በማይል የኤኮኖሚ እድገት ፕሮፓጋንዳ ማደንቆራቸው ይጨምር ይሆናል። ሕዝብ የሚፈልገው መሰረታዊ ለውጥና የመብት መከበር ላይ የሚመሠረት መልካም አስተዳደርና የሕግ የበላይነት ግን የሚገኝ አይሆንም።

ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ መንፈስ ያረፈው የመለስ አገዛዝ ባዘጋጀው የይስሙላ ምርጫ ተወዳድሮ የሚያሸንፍበት ሁኔታ ወይንም እድል አገኛለሁ በሚል ቀቢጸ ተስፋ ላይ ሳይሆን፤ ልቡ የተሰቀለው 'እስከመቼ ይህ አገዛዝ በሥልጣኑ ይቀጥላል?' የሚለውም ላይ ሳይሆን ከዚህ አገዛዝ ግብአተ መሬት በኋላ ማን ይቀጥላል? ማን ይመጣል የሚለው ላይ መሆኑ ስውር አይደለም። ስለሆነም ሕዝብ ይሁንታውን ያልሰጠበትን የመለስን ሕገ አገዛዝ እናስከብራለን በሚል የሕዝብ ሰላም እንዲደፈርስና ማህበራዊ ደህንነቱ እንዲናጋ፤ በሕዝቡ መካከል ሽብር እንዲነዛ፤ ሕዝብ ያለውዴታው በግዴታ በወያኔ አገዛዝ ሥር እንዲቀጥል፤ ሕዝብ በጎሳና በሃይማኖት ተከፋፍሎም እንዲፋጅ፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ እንዲገፈፉ፡ ፍትህ እንዳያገኝ፡ ያለ ጥፋት እንዳሻ በካድሬዎች እንዲታሰርና እንዲንገላታ መጠቀሚያ መሆናችሁ እስከ መቼ? የሚለው ጥያቄ መነሳቱን የምትሰሙት ነው። ከሆነ አይቀር የሀገርን ድንበርና ሕዝብን ከውጭ ጠላት ጥቃት  መጠበቅ ሳይሆን የተወሰነ ቡድን ጥቅም ማስጠበቂያና የሥልጣን እድሜ ማራዘሚያ ስትሆኑ መታዘቡ የሚያሳዝን ቢሆንም ሀቅ ነውና፤ ይህ እንዲታረም የበኩላችሁን አስተዋጽዖ ማበርከቱ ሀገራዊ ግዴታችሁ መሆኑን በማስታወስ በዚህ ስምሪት እንድትካፈሉ እየቀረበላችሁ ያለውን ሀገራዊ ጥሪ በጥሞና አስተውሉት።

በሌላ በኩል ግን ሕዝብ ከልቡ፣ በፍላጎቱ ድጋፉን ሳይሰጣችሁ፤ እንደ አይን ብሌኑ ሳያያችሁ፤ የጦር ልብስና ጠመንጃ ስላነገባችሁ ብቻ ተመክታችሁ ከውድቀት የምትድኑ ከመሰላችሁና ዘላለማዊነት ስሜት ካደረባችሁ ተሳስታችኋል። የመለስ ህገ አገዛዝ ጠባቂና ተንከባካቢ ሆኖ መገኘት ከወያኔነት ተለይቶ የሚታይ እንዳልሆነ መገንዘቡ ይጠቅማል እንጂ አይጎዳችሁም። በናንተ ትከሻ እየተረማመደ የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም የሚፍጨረጨረውና እናንተም ለዚሁ አላማው እያገለገላችሁት ያለው የመለስ አገዛዝ፣ ሥልጣን ቋሚ ርስት አለመሆኗን አልተገነዘበም። በሚያፈሰው የሕዝብ ደም በመስከሩ አይኑን አሳውሮታል፤ ሕሊናውን ደፍኖበታል። በአምባገነንነት ነግሶ የነበረው የደርግ አገዛዝ ተንኮታኩቶ እንደወደቀ ሁሉ ይሄም መውደቁ የማይቀር መሆኑን ለመገንዘብ አልተቻለውም። ነገር ግን በምንም አይነት ከታሪክ ውዳቂነቱ ልታስጥሉት አትችሉም። ከላይ ጀምሮ በተለያዩ የሥልጣን እርከን የተሰገሰጉባችሁ ሕዝብን በማገልገል ፈንታ የራሳቸውን ጥቅም አሳዳጆች ናቸው። በሙስና ከመጨማለቃቸውም በላይ የሕዝብን መብትና የሥልጣን ባለቤትነት መርገጣቸው የጥፋት መልዕክተኛ መሆናቸው ለዚሁ የዳረጋቸው ናቸውና ለሌላው በቆፈሩት የመቀበሪያ ጉድጓድ ውስጥ እነሱም ራሳቸው ከመግባት ምንም ኃይል አያስጥላቸውም። ይህ አይነት አባዜ የደርግ ሠራዊትም ተጠናውቶት እንደነበርና ግና ከመበታተን፣ ለጀብዱነት የተሸለመውን ኒሻን በትከሻው አንጠልጥሎና ማዕረጉኑም እንዳነገበ ከእስር፣ ከመንገድ አዳሪነትና ለማኝነት ብሎም ከስደት አለማምለጡ ለናንተም ማስጠንቀቂያ ሊሆናችሁ የሚገባ ጉዳይ ነው። የጡረታችን መብት ይከበር ብሎ የኋላ ኋላ ማልቀሱ ምንም የፈየደው ነገር የለም።

የሰው ፍጡር ናችሁና፤ የሀገሪቷ ዜጎች ወገኖቻችሁ ፍትህ አጥተው ሲበደሉና በጠራራ ፀሐይ ሲጨፈጨፉ እያያችሁ እንዳላየ መሆን ሰብአዊነታችሁ የሚቀበለው አይደለምና ላለፈው ንስሃ ገብታችሁ፤ ለወደፊቱ ከድርጊቱ ተባባሪነት እንዳያስቆጥራችሁ ድምፃችሁን እንድታሰሙ፤ የሕዝብን

እንባ ለማድረቅ በሕዝብ ላይ እንድታነጣጥሩ ያስታጠቋችሁን የጦር አፈሙዝ አቅጣጫውን በሕዝብ ጠላት ላይ እንድታደርጉ ኢሕአፓ የትግል፥ የህዝብና የሀገር አድን ጥሪ ያቀርብላችኋል።

ሕዝብ እንደ ሕዝብ በቀጣይነት መኖሩ፤ ሀገርም እንደ ሀገር መቆየቷ የማይቀር ነውና በስብሶ ለሚወድቅ አገዛዝ አገልጋይ ከመሆን ይልቅ የራስን ታሪክ ተሃድሶ የሚሰጥ፤ የጀግንነት ታሪካችሁንም ለልጅ ልጆቻችሁ የምታወርሱት በጎ ተግባር ሰርታችሁ የማይቀረውን የሞት ፅዋን ለመጎናፀፍ ዝግጁ ብትሆኑ ሕዝብም ያከብራችኋል፤ ይኮራባችኋልም። አብረን በጋራ ትግል እንዲወለድ የምናደርገው የዴሞክራሲ ሥርዓት ጠቀሜታው ለናንተም ጭምር ነውና፣ ስለዚህም የጥፋት ተልዕኮ ከሆነው ቡድን ተለይታችሁ ከሱም አገልጋይነት ተላቃችሁ ከሕዝቡ ጎን ተቀላቅላችሁ ብሩህ የሆነ ሥርዓት ለማምጣት ሙያችሁን ተጠቀሙበት። ኢሕአፓም ምንጊዜም ከናንተው ጎን ይሆናልና ፈልጉት! ባጭሩ እንፈላለግ ይላችኋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በቆራጥ ትግሉ ድልን ይቀዳጃል!!
እናቸንፋለን!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France